# የምርጫውን ውጤት ተከትሎ ለወጡት አቧራ ደረቅ ሣር

# እየጐዘጐዙ የሚገኙ ፓርቲዎችን ……2

ዮናስ 03-19-15

ስለሰብአዊ መብት ከተባለ ረጂና መሪ ሆኖ የሚመጣውና የሚታየው ሂዩማን ራይትስ ዎች ነው።

ታዲያ ይህ ድርጅት በስራ ላይ በቆየባቸው 34 ያህል ዓመታት ከገነባው አለም አቀፋዊ ስምና አቅም በላይ በሚገርሙና ግራ በሚያጋቡ ወቀሳዎች የተከበበ ነው። ሲብስም የተቋሙን አለም አቀፋዊ አቅም የተገነዘቡ በርካቶች በተለይ ምዕራባዊ አደርባዮች "የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ልዕለ ሃያል" ሲሉት ይደመጣል። የሚሰነዘሩበት ወቀሳዎች ይዘትና አይነት ግን ከዚህ አቅሙ ጋር የማይመጣጠኑ "የማሞ ሌላ መታወቂያው ሌላ" አይነት የመሆናቸው እውነት በተቋሙ ዙሪያ አያሌ ጥያቄዎች እንዲነሱ አድርጓል። እያደረገም ነው፣ ወደፊትም እንደሚቀጥል እርግጥ ይመስላል።

- በሰብአዊ መብት ጥላ ስር ፖለቲካዊ አጀንዳዎችን ማራመድ፣
- ደረጃቸውን ያልጠበቁና ኢ-ስነምግባራዊ "ጥናቶች" በማሰራጨት
- ሉዓላዊነትን የሚጥሱ፣ በወገንተኝነት የሚመሩ ጣልቃ ገብነቶች በማድረግ፣
- ፖለቲካዊ ተቃውሞዎችን በማገዝና በማስተባበር፣
- የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን ኢጋኖና አዛብቶ በማቅረብ፣
- ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲሰፍን በሚል ሽፋን የመንግስታትን ስልጣን በመሻማትና ሀገራዊ ሰላምን በማደፍረስ፣
- ግለሰባዊ የፖለቲካ አቋሞችን በማራመድ፣
- ሀገራትን በአድልኦ በመመልከት፣
- ምንጫቸው ያልተጣሩ የገንዘብ ምንጮችን በመጠቀም ወዘተ - - - ወንጀሎች በየአደባባዩ ይከሰሳል። በእሥራኤልና ፍልስጤም ጉዳይ፣ የጆርጂያና ዩክሬን አመፆች፣ የሰሜን አፍሪካና የመካከለኛው ምስራቅ የእርስ በርስ ግጭቶችና አመጾች፤ የምርጫ 97 በኢትዮጵያ ግርግሮችና የቀለም አብዮት ሙከራዎች፣ በመሬት ወረራና የሃይማኖት ነፃነት ስም ኢትዮጵያ ላይ የወጡ ሪፖርቶች፣ ወዘተ የተቋሙ ከላይ የተመለከቱ ወቀሳዎች ሁነኛ ማሳያዎች ሲሆኑ

ታዲያ ይህ ተቋም በየጊዜው በየሚዲያው ከሚያወጣቸው የሰብአዊ መብት ጥሰቶችና ተዛማጅ ጉዳዮች ሪፖርቶች እኩል እጅግ በጣም ብዙ ሀገራት ከቀላል እስከ ተደራጀ መልስ ሰጥተውታል። እየሰጡትም ነው። (በነገራችን ላይ የተቋሙ እርግጫ የበዛባቸውና ሉዓላዊነታቸው የተደፈረባቸው ሀገራት ይህን ተቋም ለመቃወም ሲሉ ልዩ ግብረ ሃይል ማቋቋማቸው በአለማችን ያለ እውነታ መሆኑ አፅንኦት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ይመስለኛል)

ሀገራችንም በተለይ ከምርጫ 97 በኋላ በተለያዩና በማይመለከተው ይልቁንም ከሰብአዊ መብት ጋር በማይገናኙ ጉዳዮች ላይ ሁሉ የዚህ ተቋም ሰለባ መሆኗን እንደቀጠለች ነው። ስለሆነም እንደ ሂዩማን ራይትስ ዎች ያሉ ድብቅ ፖለቲከኞችና፣ የጥላቻ ፖለቲካ አራማጆች ለየትኛውም ሀገር ስጋት የመሆን አቅማቸው ከፍተኛ ነው። በተለይም የሚሰማቸው ህዝብ ካገኙና በርከት ያሉ አደርባዮች ካገዟቸው የፖለቲካ ስርዓቱን እስከማናጋት ይደርሳሉ፤ የሀገርን ቅኝት ያዛባሉ።

ጉዳዩን ያስነበበን አቶ ዳንኤል የተባለ ብሎገር/ ጦማሪ ነው። "ሂዩማን ራይትስ ዎች ህዝቡ ለምርጫ እንዲመዘገብና እንዲመርጥ "ይደረግበት የነበረውን ግፊት'' በሪፖርት ሲገልጽ እንዲህ በሚል መንገድ ነበር። "ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግን አልመርጥም የሚል ህዝብ እንዳይበዛ በመስጋቱ በሚያዝያ እና በግንቦት ውስጥ ባለሥልጣናትና ሚሊሻዎችን (በአማርኛ ታጣቂ የሚባሉትን) ቤት ለቤት በማሰማራት እንዲመዘገብና ገዢውን ፓርቲ እንዲመርጥ ሲያደርግ ነበር'' አቶ ዳንኤል በዚህ መልኩ የድርጅቱን ሪፖርት በአጭሩ ከገለፁ በኋላ ሶስት ጥያቄዎችን ያነሳሉ።

1. በሚያዚያና ግንቦት የመራጮች ምዝገባ ነበርን?
2. በአዲስ አበባ ኸረ እንዲያውም በሌሎች የኢትዮጵያ ከተሞችስ ሚሊሻ የሚባል ነገር አለን?
3. ከአዲስ አበባ ነዋሪዎች መካከል ፖሊስን በስህተት እንኳን ታጣቂ ወይም ሚሊሻ ሲል የሚጠራ አንድ ሰው ይገኝ ይሆን?

የአቶ ዳንኤል ብርሃኔ መልስ አዘል ጥያቄዎች ለአለም የሚያስተላልፉት ከባድ መልዕክት ይዘዋል።

ሂዩማን ራይትስ ዎች "ትዝብቴ'' "በምርምር ያረጋገጥኳቸው'' "በጥልቅ ጥናቴ ያገኘዋቸው'' እያለ ወዘተ....ለአለማችን ግዙፍ ሚዲያዎች የሚያቀርባቸውን ዘገባዎች "የምዕራባውያን አደርባዮች'' ውጤቶች ስለመሆናቸው እንድናረጋገጥ ያደርጉናል።

የሠማያዊ ፓርቲው ሊቀመንበር ኢንጂነር ይልቃል ጌትነት ሰልፍ ባደረጉ ማግስት በያለበት ይነከሩ ነበርና በፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ሞጋች ፕሮግም ላይ ሊሞገቱ ቀረቡ፡፡ ከሞጋቻቸው የቀረበላቸው የመጀመደሪያ ጥያቄ "ፓርቲያችሁ የሚወክለው የትኛውን ማህበረሠብ ነው?" የሚል ነበር እሣቸውም ሲመልሱ እንቱ የተሠኙበትን ከአብዮቱ በፊት የነበረ ልደት ቀናቸውን በመዘንጋት፤ አልያም አንቱ ተሠኝተው አንቱ ያሰኛቸውን ከአብዮቱ ዘመን በፊት ወላጆቻቸውን ትተው ከ66ቱ አብዮት በፊት የነበረው ዜጋን ፓርቲያቸው እንደማይወክልና የአዲሡ ትውልድ ፓርቲ ለአዲሡ ትውልድ መሆኑን ተረኩ፡፡ በርግጥ ይህን ጥያቄ በዚህ መልክ ከመለሡ በኋላ በሞጋቻቸው ለቀረበላቸው ተከታታይና የሚሞግቱ ጥያቄዎች ሊቀመንበሩ ሲመልሱ ቆመንለታል የሚሉትን አዲስ ትውልድ ትተው አልያም ወጣቱን ነጥለው ሣይሆን ስለህዝብ ማውራታቸው ፓርቲያቸው ግራ የተጋባ እና ፕሮግራም አልባ ስለመሆኑና መሪዎቹም ግራ የተጋቡ የሥልጣን ጥመኞች መሆናቸውን ያረጋገጠ ነው፡፡ ይህንኑ

የሙግት መድረክ ተከትሎም በተለያዩ ጋዜጦች ላይ የፓርቲያቸው አባሎች ሊቀመንበሩ ላይ የነቀፌታ መአቱን ማውረዳቸው የፓርቲውን መርህ የለሽ አቋም የሚያረጋግጥ ነው፡፡

በምርጫ 97 ዋዜማ ላይ መስቀል አደባባይ ላይ የፈሠሠውን ወጣት የተመለከቱት የቀለም አብዮት አራማጆች ምርጫው እንደ ዩክሬን ጆርጂያው ብርቱካናማ አብዮት ይቀየር ዘንድ በታዛቢ ቡድን እና በግብረ ሠናይ ድርጅት ሥም በላኳቸው ቅጥረኛ ኃይሎች በኩል ከቅንጅቱ አመራር አካላት ጋር መከረውና ዘክረው ሲያበቁ ሥራቸውን ምርጫው ገና ሣይካሄድ ቅንጅቱ የአሸንፈናል አዋጅ እንዲያሥነግር በማድረጋቸው ብልሁ መንግስትና ገዢ ፓርቲ በነበረው በሳልና ጥበብ የተሞላ ፖለቲካዊ ልምድ የህዝቡ ጨዋነት ታክሎበት ባይቀዘቅዝ ኖሮ ይደርስ የነበረውን ጥፋት መገመት አይከብድም፡፡ ይህ የከሸፈባቸውና ግርግር ባዩበት የማይጠፉት የቀለም አብዮት አራማጆች በለጋሽ ሃገራት ሥም ከሰሞኑ በሃገር ውስጥ ገብተው ሠማያዊ ፓርቲን ሊጠልፉ እያመቻቹት መሆኑን እራሣቸው ኢንጂነር ይልቃል ጌትነት የሠማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር መናገራቸውን ከዘገባዎች አደመጥን፤ አነበብን፡፡

ከኢትጵያ ጋር ባለው ግንኙነት በውጭ የሚገኘው ኃይል በአጠቃላይ በሁለት ተከፍሎ ሊታይ የሚችል ነው፡፡ አንደኛው ክፍል የኢትዮጵያን ክፋት የማይመኝና በጀመርነው የልማትና የዴሞክራሲ ጉዞ እንዲሳካልን የሚፈልግ ነው፡፡ ይህ ክፍል በሁሉም የዓለም ማዕዘናት የሚገኝ ሲሆን አንዳንዱ ከልማታዊና ዴሞክራሲያዊ አቅጣጫ ሌላው ከልማታዊ አቅጣጫ፣ ሌላው ደግሞ ከሊበራል አስተሳሰብ በመነሳት ነጻነታችንን አክብሮ ቢቻል ከየራሱ አቋም ጋር በሚጣጣም አቅጣጫ እንድንጓዝ የሚፈልግ ነው፡፡ በመሆኑም የአመለካከት አንድነትም ሆነ ልዩነት ቢኖርም ባይኖርም ከዚህ ክፍል ጋር በሰላምና በጋራ ጥቅሞች ዙሪያ መስራት እንደሚቻል መቀበል ይቻላል፡፡ ከዚህ ለየት ባለ አኳኋን የሚታየው የአክራሪ ኒዮ ሊበራል ሃይሉ ሲሆን ይህም ከራሱ መጽሀፍ በስተቀር ሌላ እንዲነበብና መመሪያ እንዲሆን የማይፈልግ፣ የራሱን መመሪያ በሌሎች ላይ በውድም በግድም መጫን የሚፈልግ ነው ተብሎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ በመሆኑም ስለ ዓለም አቀፍ የቀለም አብዮት ስናስብ አንቀሳቃሽ ሞተሩ ይህ ሃይል እንደሆነ ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡

ይህ አክራሪ የኒዮ ሊበራል ሃይል ዓለምን በራሱ አምሳል ለመቅረጽና ለእርሱ ብቻ የምትመች እንድትሆን ለማድረግ ሁሉንም ዓይነት ማስገደጃ መሳሪያዎች መጠቀም የለመደ ነው፡፡ የማስገደጃ መሳሪያ ከመጠቀሙ በፊት በማባበል ከተሳካለት በዚሁ ተማምኖ የበላይነቱን ያረጋግጣል፡፡ ይህ አልሰራ ካለው ደግሞ ሃይልን ከዚህም አልፎ ቀለም አብዮትን እንደ ዋነኛ ማስፈጸሚያ ይጠቀምበታል፡፡ በዚህ ምክንያት ትክክለኛም ይሁን የተሳሳተ የራሳቸውን አቅጣጫ መከተል የመረጡ አገሮች ሁሉ ነጻ መንገድን በመምረጣቸው ብቻ ይህን የመሰለው አብዮት ሲቀጣጠልባቸው ማየት የተለመደ ሆኗል፡፡ የቀለም አብዮት አብዛኛውን ጊዜ ከምርጫ ወቅቶች ጋር ተያይዞ የሚቀሰቀስ ቢሆንም አልፎ አልፎ ከምርጫ ውጭ ከሚከሰቱና በቀለም አብዮተኞች ዘንድ መልካም አጋጣሚ ተደርገው ከሚወሰዱ ምርጫ ነክ ያልሆኑ ቀውሶች ጋርም ተያይዞ የሚቀሰቀስበት አጋጣሚ አይታጣም፡፡ለምሳሌ በቻይና ከአሎምፒክ በፊት በቲቤት ጥያቄ ሽፋን የተቀሰቀሰው የክሪምሰን አብዮት ሰሞንኛ የነበረው የዩክሬን አብዮትና በሃገራችንም ከአክራሪነት ጋር ተያይዞ ለመሞከር የታለመውና ግና በጥንስሱ የተቀጨውን አብዮት የመሳሰሉቱ በዚህ ክልል እንደሚታዩ በመስኩ ጥናት ያደረጉ ሰዎች ይገልጻሉ፡፡

የተፈጥሮ ሃብትን በትክክለኛ መንገድ ለህዝብ ጥቅም መዋሉን በመከታተል ለሀገራት እውቅና የሚሰጥ ‹‹ዘ ኤክስትራክቲቭ ኢንዱስትሪስ ትራንስፓረንሲ ኢንሺየቲቭ (the extractive Industries Transparency initiative - EITI) የተባለ አለም አቀፍ ተቋም አለ፡፡ ይህ ተቋም የተመሰረተው በቀድሞው የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስስቴር ቶኒ ብሌር እ.ኤ.አ. 2003 ነው፡፡ ዋና አላማውም በተፈጥሮ ዘይት፣ ቢጋዝና በማዕድን ልማት ዘርፍ ግልፅነት በማስፈን ሙስናን መዋጋት ሲሆን አባላቱም መንግስታት ሲቪል ማህበረሰቡና የማዕድን ኩባንያዎች ናቸው፡፡

ኢትዮጵያም የዚሁ የዓለም አቀፍ የማዕድን ኢንዱስትሪ ግልፅነት ኢኒሸየቲቭ አባል ለመሆን እ.ኤ.አ በ2010 ጥያቄ ብታቀርብም "መንግስት ያወጣው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ ሲቪል ማህበረሰቡን የሚያሰራ አይደለም" በማለት ጥያቄውን ውድቅ አድርጎት እንደነበር ይታወሳል፡፡

ይህንኑ በመከተል ኢትዮጵያ ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች ያወጣችው አዋጅ እራሷን ከዓለም አቀፉ አክራሪ የገበያ ኃይል ለመከላከልና እራሷን ከቀለም አብዮት ለመታደግ እንዲቻላት እንጂ በእርግጥም ስራንና ድጋፍን እንዲሁም ትክክለኛውን የሲቪል ማህበረሰብ አባላት ስራዎች ታሳቢ አድርገው ለመጡ ሃይሎች ሁሉ በሯ ክፍት እንደሆነ በተደጋጋሚ ከመግለፅም በላይ ፤ ተቋሙ በነበረው የተሳሳተ ግንዛቤ ጥያቄውን ለረጅም ጊዜ ሳይቀበል ቀርቷል።

በመሆኑም ኢትዮጵያን በተመለከተ ለኢንሸየቲቩ ያቀረበው ጥያቄ ውድቅ ሆኖ ኢትዮጵያም ሂዩማን ራይትስዎች በሚለጥፍባት ሳይሆን በተግባር ያስመሰከረቸው ስራ ተገልፆ ጥያቄዋ ተቀባይነትን አግኝቷል፡፡

ዘገባውን ያስነበበው የቀለም አብዮት አራማጅ ሃገራት አራጋቢና ባለቤትነቱም ለገበያ አክራሪነት የማይፈነቅሉት ድንጋይ የሌላቸው ምዕራባዊያን ቱጃሮች የሆነው ፋይናንሻል ታይምስ ነው ።ጥናት አደረገ የተባለው ተቋም ደግሞ የምዕራባዊያኑ የገበያ አክራሪ ኃይሎች መፈልፈያ የሆነው የኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ ነው፡፡ ይህ ተቋምና ጋዜጣ በአይጥ ምስክሯ ድንቢጥ መርሆ ስለቀለም አብዮት ሰራን ያሉትና ያስነበቡን ነገር እስከዛሬ የት ከርመው ነው የሚያሰኝ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም ጥናታቸውና ዘገባው የተመለከተው ሃገር የሚያስደንሰው ብሄራዊ መዝሙራችንን (የህዳሴ ግድባችንን) በተመለከተ ስለሆነ፡፡ "ታላላቅ ግድቦችን በመስራት ላይ የሚገኙ ታዳጊ ሃገራት ለከፍተኛ ችግር ተጋልጠዋል፡፡" በሚል ዳርዳርታ ኦክስፎርድ ዩንቨርስቲን ጠቅሶ ዘገባውን የጀመረው ፋይናንሻል ታይምስ በኢትዮጵያ ካለው የግልገል ጊቤ ሶስት ጀምሮ እስከ ብራዚሉ የአማዞን ቤሎሞንቴ ያሉ የግድብ ፕሮጀክቶች “በርካታዎችን ከመኖሪያቸው የሚያፈናቅሉ ለብዝሃ ህይወት አደጋም እንዲጋለጡ የሚያደርጉ ናቸው” ሲል ገልጧል፡፡ ቀጥሎም የቀለም አብዮትን ሙከራ የሚመዘገበት እና የጠቀሳቸውን ሃገራት የልብ ትርታ የሚያዳምጥበትን ምክርም ሰጥቷል፡፡ በእርግጥም ምክር ተኮር የሆነው መፈተሻ በሃገር ውስጥ ፅንፈኛው በተደጋጋሚ የተባለና እየተባለ የሚገኝ ነው፡፡ ይኸውም ‹‹ለህዝቡ የምታስቡ ከሆነ ገንዘቡን ለሌላ ተግባር አውሉት›› የሚል ነው፡፡

የህዳሴው ግድብ በተጀመረና ‹‹እኛው ባለሙያ፣ እኛው የፋይናንስ ምንጭ፣ እኛው ግንበኛና መሀንዲስ ሆነን እንሰራዋለን›› አዋጅ ሰሞን የተባለው ይህ ምክር ተኮር የልብ ትርታ ማዳመጫ፣ ዛሬም እየተባለለት ሲሆን በአንፃሩ ደግሞ መስራት

መቻላችንን በሚያረጋግጥ ደረጃ ላይ የደረሰው የህዳሴ ግድብ እየገሰገሰ ነው፡፡ ያም ሆኖ ግን "የትም አይደርስም" የሚለውን የግብጽ ፕሮፓጋንዳና ፀረ ልማታዊ አስተሳሰብ ተንተርሰው የተነዙት ወሬዎች መክሸፋቸው በተረጋገጠበት በዚህ ሰዐት ግብፅ የጀመረችውን ኢፍትሃዊና ያረጀ ያፈጀ ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ከመጪው ምርጫ ጋር አያይዘው ጉዳዩን ለቀለም አብዮት የሚያመቻምቹ ፅንፈኛ የገበያ አክራዎችና የዜሮ ድምር ፖለቲካ ስብስቦች ያሻቸውን ቢሉም የትም የማያደርሳቸው እንደሆነ የሚያረጋግጡ ወሳኝና በግልፅ የሚታዩ ሁነቶች ሞልተዋል፡፡

ጉዳያችን ግልጽ ይሆን ዘንድ ወደኋላ መለስ ብለን ደግሞ የቀለም አብዮት አጋፋሪዎቹን የምርጫ 2002 የቀለም አብዮት እንቅስቃሴ እናስታውስ። የመጀመሪያ ተኲስ ሂውማን ራይትስዎች ‹‹በኦጋዴን ባልታወጀ ጦርነት በጅምላ ጭፍጨፋ እየተካሄደ ነው›› በማለት ባቀረበው የሰብአዊ መብት ጥሰት ውንጀላ መልክ የቀረበ ነበር፡፡ በመቀጠልም የአሜሪካን የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት፣ አምነስቲ ኢንተርናሽናል፣ የጋዜጠኞች መብት አስጠባቂ ነን ባይ ተቋማት ወዘተ… ከየጠቅላይ መምሪያቸው ተመሳሳይ ውንጀላ በማሰማት ህብረተሰቡን ከሚያየውና ከሚያውቀው እውነታ በተለየ የፈጠራ ወሬ ቅሬታ እንዲያድርበትና ለወጠኑት የቀለም አብዮት በመሳሪያነት የሚያገለግል እንዲሆን መንቀሳቀሳቸው አይዘነጋም፡፡

ምርጫው ከታወጀ በኋላ ደግሞ ኢንተርናሽናል ክራይስስ ግሩፕ የተባለው ድርጅት ‹‹በኢትዮጵያ ፌደራሊዝምና መድብለ ፓርቲ ስርዓት ግንባታ ሂደቱ ከሽፏል፡፡›› የሚል ሪፖርት በማቅረብ አስቀድመው በተሰነዘሩት የማጥቃት እርምጃዎች ላይ ተደማሪ ስራ ለመስራት ሞከረ፡፡ "ትንቢት ይቀድም ለነገር" እንዲሉ ይህ ድርጅት በዚህ ብቻ ሳይወሰን  መድረክ የተባለው ድርጅት ገና በእርግዝና ደረጃ እያለ ‹‹ብቸኛው የኢትዮጵያ መድህን መድረክ ነው›› የሚል አቋም በግላጭ በማራመድ የሀገር ውስጥ የቀለም አብዮቱን ከንፍ ማስተዋወቅ ጀመረ፡፡ ይህንኑ ተከትሎም ብዙዎቹ የቀለም አብዮት አራማጅ ተቋማት በአንድ በኩል በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት ጥሰት የተስፋፋ በማስመሰል፣ በሌላ በኩል እውነትም መድረክ የተባለው ድርጅት ብቸኛው የአገራችን መድህን እንደሆነ በማስመሰል ያልተቆጠበ  የቀለም አብዮት ውትወታ አደረጉ።ሆኖም ህዝቡ ከመሰረታዊ የዴሞክራሲና የሰላም ጥቅሙ በመነሳት መመዘን  በመቻሉ ለሰላም እንጂ ለአመፅ ቦታ እንደሌለው በማያዳግም ሁኔታ ማረጋገጥ መቻሉና ይህም በውጭም በውስጥም ያሉ የቀለም አብዮተኛ ሃይሎችን ተስፋ የሚያስቆርጥና የሚያስከፋ መሆኑ አልቀረም፡፡

በዚህ የተስፋ መቁረጥ ሁኔታ ውስጥ የገባው የውጭው የቀለም አብዮተኛ ሃይል  ጊዜ ጠብቆ ምርጫ 2007 እየታቀረበ በሄደበት በአሁኑ ጊዜ በግላጭ የምርጫውን ውጤት የማስቀየር ፋይዳ ይኖራቸዋል ብሎ ያመነባቸውን ከባድ የፕሮፓጋንዳ መሳሪያዎች ወደመጠቀም አምርቷል፡፡  እራሳቸውን በተለያዩ የሰብዓዊ መብት ቅፅሎች አስውበው ማቅረብ የለመዱት ዓለም አቀፍ መያዶችም ከየጎራቸው ተጠራርተው  ሰፊ ዘመቻ ለማካሄድ በማሟሟቅ ላይ መሆናቸው የሚያሳብቁ መግለጫዎች እየተስተዋሉ ነው፡፡

ከውጭና ከውስጥ በተቀናጀ አኳኋን በመካሄድ ላይ ያለው ሰፊ የፕሮፖጋንዳ ዘመቻ አላማው ድንገት የሚቻል ቢሆን በአንድ ወቅት ሊካሄድ ለታሰበው የቀለም አብዮት ምቹ ፖለቲካዊ ሁኔታ ለማንጠፍ ነው፡፡

የቀለም አብዮት ሃይሎች በኢትዮጵያ እጃቸውን አስገብተው እንዲፈተፍቱ የሚያደርጋቸው ዋናው ነገር በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ እጦት አይደለም፡፡ ዴሞክራሲ ሁለት አስርት አመታት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በአስተማማኝ መሰረት ላይ ተገንብቷልና፡፡ ጉዳዩ ሰብዓዊ መብት የማስከበር አስፈላጊነት የቀሰቀሰው አይደለም፡፡ ኢትዮጵያ የውጭ ጣልቃ ገብ ሳትጠብቅ በህዝቦቿ ትግል ሰብአዊ መብትን አስከብራለችና፡፡ ጉዳዩ የነፃ ገበያም አይደለም፡፡ በኢትዮጵያ ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ስፋትና ፍጥነት የነፃ ገበያ ስርዓቱ ብቻ ሳይሆን የሥርጭቱ ዋነኛ አንቀሳቃሽ የሆነው የግል ሴክተር በልማታዊ አቅጣጫ እየተፈጠረ ነውና፡፡ ስለሆነም ለቀለም አብዮተኞቹ ጣልቃ ገብነት መሰረቱ ይህን ሂደት የፈጠረውና ያስቀጠለው ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ሃይል ሃገሪቱን ይምራት ወይስ እነርሱ እንደልባቸው የሚያሽከረክሩት ተላላኪ ኪራይ ሰብሳቢ ሃይል ስልጣኑን ይያዘው የሚለው ነው፡፡

በክፍል አንድና በዚህ ትርክት  በተመለከተው አግባብ የዩክሬን የፖለቲካ ቀውስ የተጀመረው የዩክሬን ፕሬዝዳንት የነበሩት ያናካሾች አሜሪካና የአውሮፓ ህብረት መራሽ በሆነው የቀለም አብዮት ስልጣናቸውን እንዲያጡ በመደረጉ ነው፡፡

አሜሪካ ከዩክሬን ግዛት ያላትን ርቀት ለተመለከተ የአሜሪካን ፍላጐት ግራ የሚያጋባ ከመሆኑም በላይ ለሩስያ ፌዴሬሽን ያላትን አነስተኛ ግምትና ንቀት ያሳያል፡፡ አሜሪካ በትራንስ አትላንቲክ ተብሎ በተሠየመ ስምምነት በአውሮፓ ህብረት ጀርባ ወደ ሩሲያ መጠጋቷ ምናልባትም የሩሲያን ፌዴሬሽን ለማፍረስ የያዘችውን የረጅም ጊዜ እቅድ አንዱ ማሳያ ተደርጐ ሊወሠድ ይገባል፡፡

በዩክሬን የተፈጠረው ፍጥጫ መነሻው በአውሮፓ ህብረትና በሩሲያ ፌዴሬሽን መካከል በተነሳው የጂኦ ኢኮኖሚክ አሠላለፍ ውስጥ ዩክሬን ሊኖራት ስለሚችለው እጣ ፈንታ ለመወሠን የተወጠነ መሆኑን በሚገባ ከላይ ማጠየቅ ችለናል፡፡

የአውሮፓ ህብረትና አሜሪካ የምስራቅ አውሮፓ ህዝቦች በራሳቸው ያላቸውን ነፃ የመወሠን መብትን ከግምት ሳያስገቡ የህዝቡን የመወሠን መብት ደፍጥጠው ወደ ግልጽ የኢኮኖሚና የወታደራዊ ግጭት ማምራታቸውን ማጠየቂያዎቻችን በሚገባ አሳይተውናል፡፡ ከአውሮፓና አሜሪካ የሞቱት ዜጐች ቁጥር ባይታወቅም የዩክሬን ዜጐች ግን  በየእለቱ የመርገፋቸውም እውነት ሊሠመርበት የሚገባው የቀለም አብዮቱ “ትሩፋት” ነው፡፡

የአውሮፓ ህብረትና አሜሪካ በዩክሬን ፖለቲካ ውስጥ ከላይ በተመለከተው አግባብ ዘልቀው በመግባት ህዝቡን ደግሞ አታክተው ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ የዜሮ ድምር ፖለቲካ ጨዋታቸውን ዛሬም አላቆሙም፡፡

በአሜሪካና በአውሮፓ ህብረት የአንድን ሃገር የወደፊት እጣ ፈንታ የመወሠን ህገ ወጥ እርምጃዎች የተነሳ በተቀሠቀሠው የፖለቲካ ቀውስ ዜጐች በአደባባይ ሲረሸኑ፣ ከመኖሪያ ቀያቸው ሲፈናቀሉ፣ ህፃናት በአስከፊ ቅዝቃዜ ውስጥ ወድቀው ህይወታቸው ሲቀሠፍ መመልከት ልብ ይሏል፡፡ በሞትና በህይወት መካከል የሚገኘው መላው የዩክሬን ህዝብም አሁን ድረስ በአውሮፓ ህብረትና አሜሪካ ምርጫ በተቀመጠለት መንግስት የግፍ እዳውን እየከፈለ መሆኑንም ስለ ድህረ ምርጫ 2007 አቧራና ደረቅ ሳር የመጐዝጐዝ ጅምር ያጤኗል፡፡

የሠማያዊው ሊቀመንበር ከሃገረ አሜሪካ ጥሪ የተደረገላቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በአዲስ አበባ የሚገኘው የአውሮፓ ህብረት የሠማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበርን በወቅታዊ የምርጫ ሂደት እንቅስቃሴና በምርጫው ሂደት እያጋጠሙ ያሉ ችግሮችን፣

የፓርቲው አማራጭ ፖሊሲዎችና የአንድነት አባላት ወደሠማያዊ በመምጣታቸው ጉዳይ እና ሌሎችም ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ እንዳነጋገሯቸው ሠንደቅ የተባለው ሳምንታዊ ገዜጣ ፓርቲውን በምንጭነት ጠቅሶ ከሠሞኑ ካሠፈረው ዘገባ መረዳት ተችሏል፡፡ አሁን ጉዳዩ ምንድነው? ምንስ ግንኙነት አለው? የሚለውን ጥያቄ መመለስ የሚቻል ይሆናል፡፡ መመለስም ብቻ ሳይሆን የሚነገድበት የሃገሬ ህዝብም እንደዩክሬን አደባባይ ወጥት ፍዳውን ሲበላ ከመኖር የሚታደገውን ስልትም የሚወጥንበት እንዲሆን ይጠበቃል፡፡

ልክ እንደ ዩክሬን አሜሪካ ከኢትዮጵያ ያላትን ርቀት ለተመለከተ፤ ጉዳይዋ ልክ በትራንስ አትላንቲክ እንደተሠየመው ስምምነት በሠብአዊ መብቶች ስምምነት ለጉዳይዋ ባሠማራቸው የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ጀርባ አዲስ አበባ የመጠጋት አስቀድሞ የነበረ እና ምርጫ 97 የከሸፈውን ፍላጐት ማንቀሳቀስዋ ቢሆንስ? ፡፡ በምርጫ 97 ወቅት አንዴ ብርሃኑ ነጋን ሌላ ጊዜ ደግሞ ዶ/ር በየነን በአውሮፓ ህብረት የታዛቢ ቡድን ጀርባ ላይ ተንጠልጥላ እንዳሰላቻቸው ሁሉ ለምርጫ 2007ቱ አባሯ ኢንጅነሩን ልታሠላው ቢሆንስ? የአውሮፓ ህብረቱስ በገዛ ጉዳያችን ኢንጅነሩን ጠርቶ የማነጋገሩ ሚስጥራት ከላይ ሊሠበስቡበት እና የገበያ አክራሪነትን ሊያስፋፋበት ያሠሉት ሁሉ እንዳልሆነ ሆኖ ለልማት በመዋሉ እና የሩቅ ምስራቅ ሃገሪቷን ቻይና በእጅ አዙር ለመድፈቅ የዜጐቻችን ደም መገበር ቅድሚያና የግድ ብሏቸው ቢሆንስ? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው፡፡ ጠይቀንም ዝም ሳይሆን መልሱን እና የምርጫ 2007ን ቀመር በዩክሬን የሆነውን ሁሉ መነሻ ከማጤን መጀመር  ነው፡፡

ይኸውም በዩክሬን ኬቭ አደባባይ ወጥቶ ሲጮህና አሁን ደግሞ ደመ ከልብ እየሆነ ያለው ህዝብ የሶስተኛ ወገኖችን አጀንዳ የሚረዳ፣ የሚተነትን እና ከሃገሩ ተጨባጭ ፖለቲካዊ ማህበራዊና ምጣኔ ሃብታዊ ኑባሬ ጋር ማዛመድና ማስታረቅ የሚችል፤ በመረጃ የተዋቀረና የተደራጀ ህብረተሠብ ያልነበረ መሆኑን የተመለከተው ጉዳይ ነው፡፡ በተለይ በእኛ ሃገር የመፈራረጅ ፖለቲካ ሠለባዎች መብዛት አኳያ የሶስተኛ ወገኖችን አጀንዳ መረዳት ማለት የገዢ ስርአቱን ትንታኔ በጥሬው መቀበልና ከስርዓቱ ጋር መሠለፍ ማለት እንደሆነ አድርገው የሚመለከቱትና በተቃራኒው የተረዱትንም የሚያሸማቅቁ መሆናቸው ቢጠበቅም ፤ጉዳዩን ከሉዓላዊነትና ከሃገር አኳያ አይቶ ፊት የመንሳትን አስፈላጊነት መጀመሪያ ማጤን ያስፈልጋል፡፡ የሶስተኛ ወገኖችን አጀንዳ መረዳት ያለብን ልክ እነሠማያዊ እንደሚሉትና ስለምርጫ 2007 ለሚያመቻቹት አቧሯ ከሚያቀርቧቸው ከላይ የተመለከቱ እና የሞራልም ሆነ የአመክንዮ ተገቢነት የሌላቸው ክሶች፣ በተመሳሳይም የገዢው ስርአትን ፕሮፖጋንዳዎች እንደወረዱ በመቀበል አይደለም፡፡ የመጀመሪያው እርምጃ የሃገራችንን ተጨባጭ የፖለቲካ፣ የማህበራዊና የምጣኔ ሃብታዊ እውነቶች በእውቀታችን ልክ መርምረን እና አይተን እውቅና መስጠትና መንሳት ነው፡፡

ሁለተኛው እርምጃ በሃገራችን ውስጥ ያለውን ነባራዊ ሁኔታዎች መካድ፣ ማህበራዊ ምስክርነት የሚሠጣቸውን ችግሮችን ወደ ጐን ማድረግ፣ በስነ አመክንዮ የሚገለጽ ስርአተ መንግስትን ጠንካራ ስራዎች እውቅና አለመስጠትና መካድ ተገቢ ያልሆኑ የፖለቲካ ሂደቶች መሆናቸውን መቀበል ነው፡፡

ሶስተኛው እርምጃ የሶስተኛ ወገኖችን አሉታዊ አጀንዳዎች መረዳትና ማመከን ማለት ገዢ ስርዓቱን መታደግ ወይም ተቃዋሚዎችን ማምከን ማለት እንዳልሆነ በሚገባ ማጤንና የእነዚህ ሃይሎችን ፍላጐት ከብሄራዊ ጥቅም አንፃር መተንተን መሆኑን ማስመር ነው፡፡

እነዚህ ሃይሎች ፍላጐታቸውን ለማሟላት የእጅ አዙር መንግስት በመመስረት የአንድን ሃገር ብሄራዊ ጥቅም እንደሚጨፈልቁ እና ጥቅማቸው ቀጣይ መሆን ካልቻለ አንድ ሃገር እንደ ህዝብና መንግስት እንዳይቀጥል አድርገው የሚበታተኑት መሆኑንም ከሠሜኑ የአፍሪካ ሃገራትና ከዩክሬን ተሞክሮ በሚገባ ማጤንም ሌላኛውና አራተኛው እርምጃና የምርጫ 2007 መረዳታችን ሊሆን ይገባዋል፡፡

ከህዝብ ያልመነጨ የፖለቲካ ስልጣን የጊዜ ጉዳይ እንጂ አንድ እርምጃ ፈቅ ወደሚያደረግ የፖለቲካ ሂደት መጓዝ እንደማያስችል ከዩክሬን በሚገባ አይተናል፡፡ ስለሆነም የነቃና የተደራጀ ህዝብ ከሆንን ምርጫ 2007 ውጤት በኋላ ሊነሳ ለታሠበው አቧራ እየተጐዘጐዘ ያለውን ደረቅ ሳር ማርጠብና በሃገራችን እጣ ፈንታ ላይ የመወሠን አቅም ይኖረናልና፣ እንረዳ፤ እንንቃ፤ እንደራጅ !! ፡፡